# የጥገኝነት ሂደት ላይ ያሉ አስፈላጊ ነጥቦች

ማንኛውም የሶስተኛ አገር ዜጋ ወይም ዜግነት አልባ የሆነ ሰው የጥገኝነት ማመልከቻ ማስገባት ይችላል :: የጥገኝነት ሂደቱን ለማድረግ ክፍት እና ነጻ ነው ::

## 1. የጥገኝነት ማመልከቻ ወይም የአለም አቀፍ ጥገኝነት ማመልከቻ

### የጥገኝነት ወይም የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካቾች

የጥገኝነት ወይም የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ማንኛውም ለመጀመሪያ ጊዜ ሆነም በድጋሚ በሚመለከተው አካል ፊት የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ያስገበ የሶስተኛ አገር ዜጋ ወይም ዜግነት አልባ ሰው ነው:: የግሪክ አገር ባለስልጣናት ሁለት አይነት የአለም አቀፍ ጥበቃ ይሰጣሉ:: ይህም የአለም አቀፍ ጥገኝነት እና የድጋፍ ጥበቃ ናቸው::

የአለም አቀፍ ጥገኝነት የሚሰጠው አንድ ሰው የትውልድ አገሩን ወይም ዜግነት አልባ ከሆነ፣ ቀደም ሲል በቋሚነት የሚኖርበትን አገር ለቆ እንዲወጣ ለተገደደ ሰው ሲሆን ይህም በብሄር፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት ፣ፖለቲካ ላይ ባለው አመለካከት ወይም በአንድ ቡድን ውስጥ በመሳተፉ ምክንያት በሚደርስበት ስደት ሳቢያ ፍርሃት ካደረበት እና ወደዛ መመለስ የማይችል ወይም የማይፈልግ ከሆነ ነው::

የድጋፍ ጥበቃ የሚሰጠው ከላይ የተጠቀሱትን የአለም አቀፍ ጥገኝነት የሚያሰጡ ቅድመ ሁኔታዎች ለማያሟላ ማንኛውም ሰው ሲሆን ይህም አገሩ ላይ ወይም ከዚህ በፊት ይኖርበት የነበረው አገር ላይ ከባድ የሆነ ጉዳት ሊደርስበት እንደሚችል የሚያረጋግጡ ተጨባጭ ምክንያቶች ካሉ በበለጠ ደግሞ የሞት ቅጣት ወይም የመገደል አደጋ፣ የቁም ስቅል፣ ስቃይ፣ ኢሰብአዊ ወይም ማንነትን የሚያዋርድ ሁኔታ የሚገጥመው ከሆነ ወይም በአለም አቀፍም ሆነ በውስጥ ግጭቶች ምክንያት ህይወቱ ወይም አካሉ ላይ አደጋ ሊደርስበት የሚችል ከሆነ ነው::

### ማመልከቻው የሚቀርበው የት ነው?

የመጀመሪያ ማመልከቻውን ለማስገባት የሚመለከታቸው አካላት መቀበያ እና ማንነትን ማረጋገጫ ማዕከላት ሲሆኑ እነዚህም በደሴቶች በኩል ለሚገቡ በሌዝቮ በሂዮ ፣በሳሞ፣ በኮ፣ በሌሮ፣ ና በኤቭሮ ይገኛሉ። ከላይ በተዘረዘሩት በታዎች ማመልከቻዎትን ካላቀረቡ በሌላ አማራጭ በማላካሳ ወይም በዲያቫታ የሚገኙት መቀበያ እና ማንነትን ማረጋገጫ ማዕከላት ማመልከቻዎትን ማቅረብ ይችላሉ:: ለአቅመ አዳም/ ሄዋን ያልደረሱ ማመልከቻ ማስገባትን በተመለከተ የሚመለከታቸው ባለስልጣናት የክልሉ የጥገኝነት ቢሮ እና እራሱን የቻለ የጥገኝነት ተቋም ናቸው ::

ማመልከቻ ማቅረብ የሚቻለው በአካል ተገኝተው ነው። ምዝገባዎትን ካላደረጉ በስደተኛና ጥገኝነት ሚኒስትር ኤሌክትሮኒክ ድህረ ገጽ ላይ ቀጠሮ በማስያዝ ማላካሳ ወይም ዲያባታ በሚገኙት በመቀበያና

እና ማንነት ማረጋገጫ ማእከላት መመዝገብ ይችላሉ::

ወደ አገሪቱ የገቡት ህጋዊ ባልሆነ ሁኔታ ከሆነ ወይም በግሪክ አገር ውስጥ የሚኖሩት ህጋዊ ባልሆነ ሁኔታ ከሆነ ወደ መቀበያ እና ማንነት ማረጋገጫ ማዕከል ይዛወራሉ። ማንነትዎን እና ዜግነትዎን የሚያረጋግጥ ከህጋዊ አካል የተሰጠ ሰነድ ከሌልዎት በመቀበልና ማንነትን በማረጋገጥ ሂደት ውስጥ እንዲያልፉ ይደረጋል። የማመልከቻው ምርመራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በዛው ማዕከል በግዴታ እንዲቆዩ ይደረጋል። ሆኖም በማዕከሉ የሚቆዩበት ጊዜ ከ ሃያ አምስት (25) ቀን የበለጠ ሊሆን አይገባም ::

በአጠቃላይ የማመልከቻዎ ምርመራ ከሃያ (20) ቀን እስከ ስድስት (6) ወር ሊፈጅ ይችላል::

**የማመልከቻዎ ምዝገባ**

የማመልከቻዎ ሙሉ ምዝገባ ውስጥ የሚጠቃለሉት ማንነትዎን የሚያመላክቱ መረጃዎች የሚከተሉት ናቸው: የትውልድ አገርዎን ፣ የአባት ፣ የእናት ፣ የባል ወይም የሚስት እና የልጆች ስም ፣ የኢሜይል አድራሻ ካለዎት ፣ አካላዊ የማንነት ማረጋገጫ መረጃዎች(Biometric Identification) ፣ የአለም አቀፍ ጥበቃ እንዲጠይቁ ያደረገዎት ምክንያቶች ሙሉ ዝርዝር፣ የመኖሪያ ወይም የቤት አድራሻ ፣ጉዳዩ እንዲመረመር የሚፈልጉት በምን ቋንቋ እንደሆነ እንዲሁም በወካይ ተወክለው መቅረብ የሚፈልጉ ከሆነ የሚገልፁ ዝርዝሮችን ያካተታል::

አካላዊ ፍተሻ ወይም የግል ንብረትን በተመለከተ ፍተሻ ሊደረግ ይችላል። በሃኪም ሊመረመሩም ይችላሉ::

ማመልከቻውን በሚያስገቡበት ወቅት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ሲነጋገሩ በሚረዱት ቋንቋ መግባባት ይችሉ ዘንድ በአስተርጓሚ አማካኝነት ስለ ሂደቱ መረጃዎች እንዲሁም እንደ የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ያልዎትን መብቶችና ግዴታዎች እንዲሁም ሂደቱ ላይ ስላሉ ቀነ ገደቦች መረጃ ይሰጡታል::

በምዝገባው ቀን ፎቶ ይነሳሉ፣ እንዲሁም የጣት አሻራዎ ይወሰዳል። ይህ ሂደት ከእርሶ በተጨማሪ ከእርስዎ ጋር ያሉ ከአስራ አራት (14) ዓመት በላይ የሆኑ የቤተሰብ አባላትን ይጨምራል። የጣት አሻራዎ በአውሮፓውያን ማዕከላዊ ቤዝ **EURODAC** (ዮሮ ዳክ) ውስጥ ይገባል:: ሌላ 《 የዱብሊን III》 ስምምነትን በፈረመ የአውሮፓ አገር ላይ የዓለም አቀፍ ጥበቃ ጠይቀው ከሆነ ወደዛው አገር ተዛውረው ማመልከቻው በዛ አገር እንዲመረመር ሊደረግ ይችላል::

《የዱብሊን III》 ስምምነት በደንቡ መሰረት የትኛው የአውሮፓውያን አንድነት አባል አገር ማመልከቻውን የመመርመር ኃላፊነት እንዳለው ይወስናል:: ይህን ለመወሰን የተቀመጡት ቅድመ ሁኔታዎች በቅደም ተከተል ከታች የተዘረዘሩት ናቸው:: ሀ) የቤተሰባዊ ትስስር ለ )ከአባል አገር በቅርብ የተሰጠ የአገር ውስጥ መግቢያ ፍቃድ ( ቪዛ )ወይም የመኖሪያ ፍቃድ ሐ) ወደ አውሮፓ ህብረት የገቡበት በህጋዊ ወይም በህገወጥ ከሆነ።

የእርስዎን እንዲሁም የቤተሰብዎን አባል ማንነት ሊያረጋግጥ የሚችል በእጅዎ ያለ የመጓጓዣ ሰነድ (ለምሳሌ ፓስፖርት) ወይም ከማመልከቻዎ ምርመራ ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላ ማንኛውም አይነት ሰነድ ማስረከብ ይኖርብዎታል::

ማመልከቻዎትን በተመለከተ የሚሰጡት ማንኛውም አይነት መረጃ ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ነው:: የመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች ሚስጥሮትን የመጠበቅ ግዴታ ስላለባቸው በማመልከቻው ምርመራ ወቅት ለሠራተኞቹ የሚሰጧቸው መረጃዎች የትውልድ አገሮ ባለስልጣናት እንዲያውቁት አይደረግም::

ለስደተኞች ጥበቃ የቆመው የተባበሩት የዓለም መንግታት ስር ያለውን ዮኤን (UNHCR) ወይም ሌሎች የህግ አገልግሎት ፣የህክምና ወይም የስነ ልበና ድጋፍ የሚሰጡ ድርጅቶችን ማግኘት ይችላሉ::

የስቃይ ሰለባ እና የመደፈር ወይም ሌሎች ከባድ ጥቃቶች ሰለባ ከሆኑ ይህንን በተመለከተ እንዲረዱ ለባለስልጣኑ አካል ሊያሳውቁ ይገባል::

በሂደቱ ላይ የጠበቃ እርዳታ ወይም እርሶ የመረጡት የሌላ አማካሪ እርዳታ የመጠየቅ መብት አሎት ( የስደተኞች መስሪያ ቤት ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ መልኩ)። ይህ ከሆነ ለጠበቃው ወይም ለአማካሪው በጹሁፍ ውክልና መስጠትና አስፈላጊ የሆነውን ፈራሚ እርሶ እንደሆኑ የማረጋገጫ ማህተም በማስመታት በጥገኝነት አገልግሎት ፊት ወክሎት እንዲቆም እንዲሁም በቃለ ምልልሶ ጊዜ አብሮት እንዲገኝ ማድረግ ይችላሉ:: ለጠበቃ ወይም ለአማካሪው የሚከፈለው ክፍያ የሚመለከተው እርስዎን ነው:: እርስዎም ሆነ የወከሉት ጠበቃ ወይም አማካሪ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚገኘውን የእርሶን ፋይል ለማየት ከፈለጉ አመልክተው ማግኘት ይችላሉ::

የጥገኝነት አገልግሎቱ የቃለ ምልልስ ቀጠሮዎን ቀን ይወስናል። እንዲሁም የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ካርድ ይሰጥዎታል። ካርዱ የሚሰራው እስከ አንድ (1) ዓመት ሊሆን ይችላል:: ይህ የአመልካች ካርድ ሁልጊዜ ሊይዙት ይገባል:: የአመልካች ወረቀት እንደ ካርድ ያለ ሲሆን በሚወጣበት ወቅት የግብር መክፈያ ቁጥርና (አፊሚ) ጊዜያዊ የማህበራዊ እና ጤና ጥበቃ የዋስትና ቁጥር (ፖይፓ) ጋር ተያይዞ ይሰጥዎታል ::

ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልገው ቡድን ውስጥ የሚመደቡ ከሆነ እና ቃለምልልስዎ ከምዝገባው ቀጥሎ ባሉት 15 ቀናት ውስጥ ከሆነ የጥገኝነት መስሪያ ቤቱ ለቃለ ምልልሶ እንዲዘጋጁ እና በሂደቱ ላይ እንዲረዳዎ ጠበቃ ወይም ሌላ አማካሪ እንዲያማክሩ በቂ ጊዜ ማለትም (እስከ 3 ቀን) ድረስ ይሰጣል። ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልገው ቡድን ውስጥ የሚመደቡት እድሜያቸው ለአቅመ አዳም /ሄዋን ያልደረሰ ታዳጊዎች፣ የቅርብ ዘመድዎን በባህር አደጋ ካጡ ማለትም (እናትና፣ አባት፣ እህትና ወንድም ልጆች ወይም ባለቤተዎን) የአካል ጉዳተኛ ከሆኑ፣ አረጋዊ ፣እርጉዝ፣ ህፃናት ልጆች ብቻውን የሚያሳድግ ወላጅ፣ ሰው የመሸጥ የመለወጥ ሰለባ የደረሰበት፣ በከባድ በሽታ ተጠቂ የሆኑ፣ የአይምሮ ወይም የስነ-ልቦና ጉዳት ያለባቸው ሰዎች፣ የስቃይ ሰለባ፣ የመደፈር ጥቃት፣ ወይም ሌላ ከባድ የሆነ የስነ ልበና፣አካላዊ ወይም ፆታዊ ጥቃት ማለትም የመገረዝ ጥቃት የደረሰባቸው ሴቶች ናቸው::

ቃለ ምልልስ የሚያደርገው የመስሪያ ቤቱ ሠራተኛ እና የአስተርጓሚውን ጾታ በተመለከተ የሚፈልጉትን ጾታ ማሳወቅ ይችላሉ:: መስሪያ ቤቱ ይህን ፍላጎትዎን ይመረምርና የሚቻል ከሆነ ይህ ፍላጎቶ እንዲሟላ ያደርጋል::

***ለዓለም አቀፍ ጥበቃ በድጋሚ የሚቀርብ ማመልከቻ***

ለአለም አቀፍ ጥበቃ በድጋሚ የሚቀርብ ማመልከቻ የሚባለው ከፖሊስ ወይም ከጥገኝነት አገልግሎት ወይም ከይግባኝ ባለስልጣን በመጨረሻ ተቀባይነት የሌለው ውድቅ ውሳኔ ከወጣ በኋላ ወይም በመጀመርያ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ካቀረቡ በኃላ ማመልከቻው ይሰረዝልኝ ብለው ካሠረዙ በኋላ በድጋሚ በአዲስ የሚያቀርቡት የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ነው ::

በድጋሚ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ የሚያቀርቡትን ማመልከቻ እና ስለ አዲስ ክስተቶች መረጃዎች በተመለከተ የመቀበል ኃላፊነት ያለው ባለ ስልጣን ከሚኖሩበት ቦታ በአቅራቢያዎ የሚገኘው የክልሉ የጥገኝነት ቢሮ እና እራሱን የቻለ የጥገኝነት ተቋም ነው:: በድጋሚ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ለማስገባት በስደተኞችና ጥገኝነት ሚኒስቴር ስር በሚገኘው የኤሌክትሮኒክ ድህረ ገጽ ላይ ቀጠሮ መዝጋት ይችላሉ::

በድጋሚ ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ካስገቡ በኋላ የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ካርድ **<u>አይሰጥዎትም</u>**::

የጥገኝነት መስሪያ ቤቱ ያቀረቡትን መረጃዎች አዲስ እና ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎ ተጨባጭነት ያላቸው መሆኑን መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል። የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ካርድ የሚሰጥዎት እና የጥገኝነት መስሪያ ቤቱ መልከቻዎን ምርመራ የሚቀጥለው በድጋሚ ያቀረቡት ማመልከቻ ተቀባይነት ካገኘ ብቻ ነው::

የስደተኞች መስሪያ ቤቱ በድጋሚ ያቀረቡትን ማመልከቻ ውድቅ ካደረገ ይህንን በመቃወም

የተቀበሉት ውሳኔ በሚያመለክተው ቀነ ገደብ ማለትም በአምስት (5) ቀን ውስጥ የይግባኝ ባለስልጣን ፊት ይግባኝ መጠየቅ ይችላሉ::

ይህ ማመልከቻዎ በሚመረምርበት ወቅት ለሁለተኛ ግዜ የአለም አቀፍ ጥበቃ ቢያቀርቡ ወደ አገርዎ ከመባረር/ከመመለስ አይጠብቅዎትም::

ለእያንዳንዱ ሰከንድ ወይም ቀጣይ የጥገኝነት ጥያቄ፣ ከማመልከቻው ጋር የሶስት መቶ (300€) ኤሌክትሮኒክ ፓራቮሎ (e_paravolo) ክፍያ ደረሰኝ ወይም ክፍያ ማቅረብ አለበት። ቤተሰብ ከሆንክ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ተመሳሳይ ክፍያ መከፈል አለበት።

## 2. **የአለም አቀፍ ጥበቃ ቃለ ምልልስ**

የአለም አቀፍ ጥበቃ ቃለ ምልልስ የሚካሄደው የጥገኝነት መስሪያ ቤቱ በሚወሰነው ቀንና ሰዓት ሲሆን

የሚካሄደውም በሚመለከተው በቂ ተክሎት ባለው የጥገኝነት መስሪያ ቤቱ ሰራተኛ ነው::

ለጥያቄዎቹ እውነተኛነት በተሞላበት መልኩ መመለስ ይኖርባችኋል:: የሚሰጡት መረጃዎች በእውነት የተፈጸሙ መሆን ያለባቸው ሲሆን ከማመልከቻዎ ጋር ተያያዥነት ያለው ማንኛውንም አይነት መረጃ ሳይደብቁ ይናገሩ:: የሰጡት መረጃ በእውነት ላይ ያልተመሰረተ ቃል ወይም ያልተፈጸመ ድርጊት ከሆነ የማመልከቻው ውሳኔ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደራል::

የጥገኝነት ቢሮ ሰራተኛ በቃለ ምልልሱ ጊዜ የሚጠይቃቸው ጥያቄዎች የሚያተኩሩት በምዝገባዎት ጊዜ በሰጡዋቸው መረጃዎች ላይ፣ ማንነትዎን የሚያረጋግጡ መረጃዎች፣ ወደ ግሪክ አገር እንዴት እንደመጡ፣ ከትውልድ አገርዎ ወይም ዜግነት አልባ ከሆኑ ቀደም ሲል በተለምዶ ይኖሩበት ከነበረው አገር ለቀው የወጡበትን እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ ለምን ወደዛ መመለስ የማይችሉበትን ወይም የማይፈልጉበትን ምክንያቶች በመሳሰሉት ርዕሶች ላይ ነው :: በቃለ ምልልሶ ጊዜ ማንኛውም ይረዳል የሚሉትን መረጃዎች መጨመር ይችላሉ ::

ለእያንዳንዱ ለአቅመ አዳም/ሄዋን ለደረሰ የቤተሰብ አባል ቃለ ምልልስ የሚደረገው ለየብቻ ነው:: ለአቅመ አዳም /ሄዋን ያልደረሱ ታዳጊዎች የሚደረግላቸው ቃለ ምልልስ የዕድገታቸውን ደረጃ፣ ስነ ልቦናቸው ላይ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ እንዲሁም ያሳለፋትን የሚጎዱ ሁኔታዎች ባገናዘበ ሁኔታ ነው::

በቃለ ምልልሱ ጊዜ አስተርጓሚ ይኖራል። ትርጉሙ የሚሆነው በሚገባዎት ቋንቋ ነው። የትርጉም አገልግሎት የሚሰጠው በነፃ ነው::

በቃለምልልሱ ላይ ላይ የጠበቃ እርዳታ ወይም እርሶ የመረጡት የሌላ አማካሪ( ሀኪም፣ የስነ ልቦና ባለሙያ ወይም የህብረተሰብ ሰራተኛ-social worker) ይዘው የመገኘት መብት አሎት:: ይህ ከሆነ ለጠበቃዎ ወይም ለአማካሪዎ በጽሁፍ ውክልና በመስጠት በስደተኞች ቢሮ ፊት ወክልዎት እንዲቆም ወይም በቃለ ምልልሶ ጊዜ አብሮት እንዲገኝ ማድረግ ይችላሉ:: ለጠበቃ ወይም ለአማካሪው የሚከፈለው ክፍያ የሚመለከተው እርስዎን ነው::

በቃለምልልስዎ ጊዜ የሚሰጡት ማንኛውም አይነት መረጃ ሚስጥራዊነቱ የተጠበቀ ነው:: ለማመልከቻዊ ምርመራ የሚሰጧቸው መረጃዎች ወደ ትውልድ አገርዎ ባለስልጣናት እዲተላለፍ አይደረግም:: ሆኖም ሌሎች የግሪክ ሀገር ባለስልጣናት እንዲያዩት ሊደረግ ይችላል::

ቃለ ምልልሱ ይቀዳል። ሰራተኛው ሁሉንም ጥያቄዎች እና መልሶች የሚያካትት ጽሁፍ (ምንባብ) ያዘጋጃል። ቃለ ምልልሱ የማይቀዳ ከሆነ የተዘጋጀውን ምንባብ በአስተርጓሚ አማካኝነት በድጋሚ በትክክል መመዝገቡን ማረጋገጥ ወይም ደግሞ እርማቶች እንዲደረጉ ጠይቀው መፈረም ይኖርባቸዋል:: ከዚያ በኋላ የቃለ ምልልሰን የምንባብ ወይም/እና የድምፅ ግልባጭ አመልክተው መውሰድ ይችላሉ:: ቃለ ምልልሱ በርቀት ሊከናወን ይችላል::

## 3. የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻን አስመልክቶ የሚወጣ ውሳኔ

ከቃለምልልሱ በኋላ የጥገኝነት መስሪያ ቤቱ የጥገኝነት ጥያቄዎ ተቀባይነት አግኝቷል፣ ወይም የድጋፍ ጥገኝነት ይገባዎታል ወይም ማመልከቻው ውድቅ ነው ሲል ውሳኔ ያስተላልፋል:: የጉዳዮ መርማሪ ማመልከቻዎትን በተመለከተ የሰጡትን ግላዊ ቃለምልልስ ፣ማመልከቻዎትን ለመደገፍ ያመጧቸውን ማስረጃዎች፣ ስለ ትውልድ አገሮ ያሉትን መረጃዎች እንዲሁም በፋይሎ ውስጥ ተካትተው የሚገኙ መረጃዎችን ሁሉ ግምት ውስጥ በማስገባት ለማመልከቻዎ ውሳኔ ያወጣል::

የጉዳዩ ምርመራ በእንጥል ላይ ሳለ **ሂደቱን ለቀው መውጣት ይችላሉ።**

ለአለም አቀፍ ጥበቃ ያቀረቡት ማመልከቻ ውድቅ ከተደረገ እንዲመለሱ ውሳኔ ይወጣል።

ከውሳኔው ሰነድ ጋር ተያይዞ በሚገባዎት ቋንቋ በቀላሉ ሊረዱት የሚችሉት ሌላ ሰነድ የውሳኔው ጭብጥ እና ውሳኔው የሚያስከትላቸውን ነገሮች የሚያስረዳ ሌላ ሰነድ ይኖራል::

ውሳኔውን በአካል ቀርበው ወይም ለእርሶ (ወይም ለጠበቃዎ) በአደራ ደብዳቤ ተልኮ ወይም በኢሜል መውሰድ ይችላሉ::

ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ ወይም የድጋፍ ጥበቃ ተሰጥዎት ሳለ ነገር ግን የጥገኝነት ጥበቃ ይገባኛል ብለው ካመኑ ከይግባኝ ባለስልጣን(በሁለተኛ ደረጃ) ይግባኝ የመጠየቅ መብት አሎት:: ይህን ማድረግ የሚችሉት የውድቅ ተደርጓል ውሳኔውን ካወጣው የክልሉ የጥገኝነት ቢሮ ወይም ራሱን የቻለ የጥገኝነት ተቋም ሲሆን ይህንንም ማድረግ የሚችሉት በውሳኔው ላይ በተጠቃለለው ቀነ ገደብ ውስጥ ነው::

የጥገኝነት ወይም የድጋፍ ጥገኝነት ተቀባይነት ካገኙ የግሪክ ዲሞክራሲያዊ የመኖሪያ ፍቃድ እና የመጓጓዣ ሰነድ ማግኘት ይችላሉ::

## 4. ስለ አለም አቀፍ ጥገኛ አመልካች ካርድ ማወቅ ያለብዎት ነገሮች

ሙሉ ምዝገባውን ካጠናቀቁ (ካስገቡ) በኋላ የአለም አቀፍ ጥገኛ አመልካች ካርድ(ደኤዲፕ) ይሰጥዎታል። ይህ ካርድ በአገልግሎት ላይ በሚቆይበት ጊዜ ጉዳይዎ እንደሚመረምርበት ሂደት ከሰላሳ (30) ቀን እስከ አንድ (1) ዓመት ሊሆን ይችላል :: የአለም አቀፍ ጥገኛ አመልካች ካርድ (ደኤዲፕ) የማመልከቻው ምርመራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በግሪክ አገር እንዲኖሩ ያስችሎታል:: ለማመልከቻዎ የወጣው ዉሳኔ ውድቅ ከሆነ የካርዱ አገልግሎት ይቋረጣል::

ያመልካች ካርድ የሚሰጠው በትንሽ ካርድ መልክ ሲሆን በኤሌክትሮኒክ መንገድ ሊመዘግብ እና ሊታደስ ይችላል::

ይህንን ካርድ በጥሩ ሁኔታ መያዝና ሁልጊዜ አብሮት መያዝ ይኖርብዎታል። ለአለም አቀፍ ጥበቃ

ማመልከቻ ማስገባትዎን የሚያረጋግጥ ሰነድ ነው::

የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ካርድ ጊዜያዊ ሲሆን የሚሰጣቸውም የተወሰኑ መብቶች እና ግዴታዎች አሉ። እንዲሁም ከመኖሪያ ፍቃድ **እኩል አይደለም::**

የአመልካች ካርድ በእስር ለሚገኙ፣ የመቀበልና የማረጋገጥ ሂደት ውስጥ ላሉ ወይም ለድጋሚ የጥገኝነት ጥያቄ ምርመራ ማመልከቻ ላስገቡ ሰዎች ማመልከቻቸው ተቀባይነት እስከሚያገኝ ድረስ አይሰጥም::

ከግል መረጃዎች በተጨማሪ የአመልካች ካርድ ላይ የወጣበት ቀን፣ አገልግሎቱ የሚያበቃበት ቀን መቼ እንደሆነ እንዲሁም ጊዜያዊ የውጭ ዜጋ የማህበረሰብ እና የጤና ህክምና መድህን ቁጥር ( ፓ. ይ.ፓ) ይገኛል::

ዋናው የአመልካች ካርድ ሁልጊዜ አብሮት ሊሆን ይገባል:: በተለይም ከጥገኝነት መስሪያ ቤት ጋር በሚያደርጉት ማንኛውም መስተጋብር ይዘው መገኘት አለብዎት:: የቃለ ምልልሱ ቀን አብሮት መሆኑን ይበልጥ አስፈላጊ ነው:: ፎቶ ኮፒ ተቀባይነት የለውም ::

የአመልካች ካርዶት የሚያገለግልበት ቀን እስከሚያበቃ ድረስ ለማመልከቻዎ ውሳኔ ወጥቶ ካልተሰጠዎ የአመልካች ካርዱ መታደስ ይኖርበታል::

የአመልካች ካርዶን ለማሳደስ የበፊቱን ካርድ ማምጣት አስፈላጊ ነው ::

የአመልካች ካርዶን ማሳደስ የሚችሉት እስካለቀበት ቀን ማግስት ድረስ ነው :: **የአመልካች ካርዶ እስከ አለቀበት ማግስት ድረስ ካላሳደሱ ያመልካች ካርዶ አገልግሎት መስጠቱን ያቆማል:: እንዲሁም ደግሞ የማመልከቻዎ ሂደት ይቆማል::**

የጥገኝነት መስሪያ ቤቱ በቴክኒክ ወይም በሌሎች የመስሪያ ቤቱን አሰራር የሚመለከቱ ምክንያቶች የአመልካች ካርዶን ሊያድስ ካልቻለ ይህንኑ የሚገልጽ ማስታወቂያ በድህረ ገጹ ላይ በማውጣት መላው ህብረተሰብ እንዲያውቅ ያደርጋል:: ይህ ከሆነ የአመልካች ካርድዎ በራሱ ይታደሳል::

## የአመልካች ካርድ እንደጠፋ ማሳወቅ

የአመልካች ካርድዎ ከጠፋ ወይም ከተሰረቀ ከጥገኝነት መስሪያ ቤት አዲስ ያመልካች ካርድ እንዲሰጥዎ መጠየቅ ይችላሉ ::

የጥገኝነት መስሪያ ቤቱ የአለም አቀፍ ጥበቃ እንዳመለከቱ የሚያረጋግጥ የአመልካች ካርድ ቁጥርዎ ያለበት ማረጋገጫ ወረቀት ይሰጥዎታል::

ይህን ወረቀት ይዘው ወደ ግሪክ ፖሊስ በመሄድ የአመልካች ካርዶ እንደጠፋ ያሳውቃሉ::

ማህተም ያለው እንደጠፋ ያሳወቁበት ወረቀት ግልባጭ ከወሰዱ በኋላ ያንን ይዘው ወደ ጥገኝነት መስሪያ ቤት በመምጣት አዲስ ያመልካች ካርድ እንዲሰጥዎ ማመልከቻ ማስገባት ይኖርቦታል:: አዲስ ያመልካች ካርድ ቢያንስ ሁለት ወር ከማለፉ በፊት አይሰጥም::

## 5)እንደ አለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ያሉዎት መብትና ግዴታዎች

### A) የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ያሉዎት መብቶች

እንደ አለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች የሚከተሉት መብቶች አሉዎት::

● በአገሪቱ ላይ በህጋዊ መንገድ እንዲንቀሳቀሱ የሚያስችል የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ካርድ በነጻ ማግኘት

● የማመልከቻዎ ምርመራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በግሪክ ሃገር መቆየት የሚችሉ ሲሆን የማመልከቻዎ ምርመራ ከመጠናቀቁ በፊት በግዴታ ወደመጡበት እንዲመለሱ ማድረግ የተከለከለ ነው::

● የተሰጥዎት የዓለም አቀፍ ጥገኝነት አመልካች ካርድ የተወሰነ የአገሪቱ ክፍል ብቻ እንዲቆዩ የሚያዝ ካልሆነ ማለትም የእንቅስቃሴ ገደብ ካልተጣለብዎ በስተቀር በመላው ሀገሪቱ ውስጥ በነፃነት የመንቀሳቀስ መብት

● በሚረዱት ቋንቋ ስለ ለማመልከቻዎ ስለሚገኝበት ሂደት መረጃ ማግኘት እንዲሁም በተለያዩ ሂደቶች ላይ ያሉትን ቀነ ገደቦች ማወቅ እንዲሁም ይግባኝ የመጠየቅ እና ማመልከቻዎን አስመልክተው የወጡ ውሳኔዎችን በተመለከተ መረጃ የማግኘት መብት

●በተለያዩ የማመልከቻው ሂደት ላይ ማለትም በመጀመሪያ እና በሁለተኛ ደረጃ በተለይም በጥገኝነት መስሪያ ቤት ፊት በሚያደርጉት ቃለ ምልልስ ወቅት በነጻ የትርጉም አገልግሎት የማግኘት መብት

● **በፍቃድዎ ወደ ትውልድ አገርዎ የመመለስ** መብት

●ለስደተኞች ጥበቃ የቆመው በተባበሩት የዓለም መንግታት ስር ካለው ዮኤን (UNHCR) ወይም ከሌሎች የህግ የህክምና ወይም የስነ ልቦና ድጋፍ የሚሰጡ ድርጅቶች ጋር የመገናኘት መብት

● ስራ የማይሰሩ ከሆኑ እንዲሁም መሰረታዊ ፍላጎቶችዎን የሚያሟላ የገቢ ምንጭ ከሌለ የኢኮኖሚ እርዳታ የማግኘት መብት

● የመጠለያ ካምፕ ውስጥ ወይም ሌላ (የግል መጠለያ የሚያቀርቡ ፕሮግራሞች ወይም ሆቴል )ውስጥ የመጠለያ ቦታ የማግኘት መብት

● የግሪክ አገር ህግ ያስቀመጠውን ቅድመ ሁኔታዎች ባሟላ መልኩ የመስራት መብት፣ ማለትም የአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻዎን ካቀረቡ ስልሳ (60) ቀን ካለፈ በኋላ እና የአለም አቀፍ ጥበቃ የአመልካች ካርድ

ካልዎት።

● የግብር ከፋይ ቁጥር (አፊሚ) የመቀበል መብት

● ሰራተኛ ከሆኑ እንደማንኛውም ግሪካዊ ዜጋ አንድ አይነት የመድህን መብትና ግዴታዎች አልዎት::

● በግዜያዊው የውጭ ዜጋ የመድህን እና የህክምና ቁጥርዎ (ፓይፓ) ተጠቅመው የመድኃኒት እና የሆስፒታል ህክምና አገልግሎት የማግኘት መብት

●ለአቅመ አዳም ወይም ሄዋን ላልደረሱ አመልካቾች የነጻ የመንግስት ትምህርት የማግኘት መብት

● ለአዋቂ አመልካቾች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት የማግኘት መብት

● የሞያ ስልጠና የመማር መብት

**ለ) የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ግዴታዎች**

እንደ አለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች የሚከተሉት ግዴታዎች አለብዎት::

● ልክ ግሪክ አገር እንደገቡ ወዲያውኑ ለአለም አቀፍ ጥበቃ ማመልከቻ ማስገባት አለብዎት::

● የአመልካች ካርዶ ሁልግዜ ከእርሶ ጋር መሆን አለበት:: የአለም አቀፍ ጥበቃ አመልካች ካርድ ጊዜያዊ ሲሆን የሚሰጣቸው የተወሰኑ መብቶችና ግዴታዎች አሉ :: እንዲሁም ከመኖሪያ ፍቃድ ጋር እኩል አይደለም::

●የአመልካች ካርዶን በሰአቱ የሚያገለግልበት ቀን ከማብቃቱ በፊት ማሳደስ ይኖርብዎታል:: ማሳደስ የሚችሉት ግፋ ቢል አገልግሎቱ ባበቃበት ማግስት ነው::

● የማመልከቻዎ ምርመራ እስከሚጠናቀቅ ድረስ በግሪክ ሀገር መቆየት አለብዎት:: ከባድ የሆነ ሰብአዊ ምክንያት ማለትም ማስረጃ ባለው ከባድ ህመም ምክንያት በሌላ አገር መገኘት እንዳለቦት የሚያረጋግጥ ነገር ከሌለ በስተቀር ከግሪክ አገር ውጪ መጓዝ አይችሉም::የመጓጓዣ ሰነድ እንዲሰጥዎ ለመስሪያ ቤቱ ማመልከቻ ማስገባት አለብዎት::

● ከግሪክ ሀገር ባለስልጣናት ጋር ማንኛውም ከማመልከቻዎ ጋር የሚያያዝ ጉዳይዎን በተመለከተ መረጃዎችን በማቅረብ እና ማንነትዎን ለማረጋገጥ በሚደረጉ ሂደቶች ላይ በትብብር መስራት ይገባዎታል::

● የቃለ ምልልስ ቀን ቀጠሮ በተያዘበት ጊዜ በጥገኝነት መስሪያ ቤት መገኘት

●ከሚመለከታቸው ባለልጣናት ጥሪ በቀረበልዎ ግዜ ሁሉ  ሳይዘገዩ በአካል መገኘት

●የመጓጓዣ ሰነድዎን ወይም ማንኛውም ሌሎች በእጅዎ ያሉ ከማመልከቻዎ  ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሰነዶችን መስጠት እና ማንነቱን የሚያረጋግጡ መረጃዎችን ማቅረብ

●የመኖሪያ አድራሻዎትንና ሌሎች አድራሻዎች ለጥገኝነት መስሪያ ቤት ማሳወቅ እንዲሁም በቀየሩ ግዜ አዲሱን አድራሻ ማሳወቅ። ይህንን በተመለከተ የመገኛ አድራሻ ለውጥን ለማሳወቅ የኤሌክትሮኒክ ማመልከቻ  ማስገባት ይችላሉ :: የጥገኝነት መስሪያ ቤቱ መልከቻዎን የሚመለከቱ ሰነዶችን ባሳወቁት አድራሻዎች( የመኖሪያ አድራሻ፣ ኢሜል ) በመጠቀም ይልካል::

● ከማመልከቻዎ ምዝገባ በኋላ በግሪክ ከአገር የተወለዱ ልጆችን ለማስመዝገብ የልደት ምስክር ወረቀታቸውን ይዘው ወደ ጥገኝነት መስሪያ ቤት መምጣትና ማስመዝገብ ይኖርቦታል::

●በተለያዩ የማመልከቻው ምርመራ ሂደቶች ላይ ሳሉ ከሚመለከታቸው ባለስልጣናት የሚሰጡትን ቀነ ገደቦች ያክብሩ :;

●ከመንግስት የሚወስዱት ማንኛውም አይነት ድጎማ ካለ እውነተኛ የኢኮኖሚ ሁኔታዎን አይደብቁ::

● በመቀበያ እና ማንነት ማረጋገጫ ማዕከላት የመጠለያ ካምፕ ውስጥ ወይም ሌላ የመጠለያ ቦታ የሚኖሩ ከሆነ መጠለያው የሚሠራበትን ደንብ ይከተሉ:: እንዲሁም ከእነዚህ ቦታዎች የሚመለከታቸውን ባለልጣናት ሳያወቁ ለቀው አይውጡ::

●ለእያንዳንዱ ሁለተኛም ወይም ቀጣይ የድጋሚ ጥገኝነት ማመልከቻ ከማመልከቻዎ ጋር አያይዘው በኤሌክሮኒክ ፓራቮሎ (ኢ ፓራቮሎ) ሶስት መቶ (300€) የክፍያ ደረሰኝ ወይም ፓራቮሎ ክፍያ ማስገባት አለብዎት:: ቤተሰብ ከሆናችሁ ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ተመሳሳይ ክፍያ መከፈል አለበት::

● ከላይ የተዘረዘሩትን ግዴታዎች አለማክበር እና ከባለስልጣናቱ ጋር አለመተባበር በተለይም ማመልከቻውን ለመመርመር አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በሚደረገው ጥረት ከባለስልጣናቱ ጋር አለመግባባትና ተባብሮ ባለ መስራት የማመልከቻዊ ምርመራ ሂደት እንዳይጠቃለል የሚያግዱ ወይም የሚያስተጓጉሉ ከሆነ ማመልከቻዎ ውድቅ እንዲሆን ያስከትላል::

● ከላይ የተዘረዘሩትን ግዳጅ አለመወጣት ይሰጡ የነበሩ ድጋፎችን (ለምሳሌ ድጎማዎች ፣ መጠለያ ወ.ዘ.ተ) እንዲቀንሱ ወይም እንዲቋረጡ ሊያደርግ ይችላል::

**6. በፍላጎት ወደ ትውልድ ሀገር መመለስ**

- ከጥገኝነት ሂደት ወጥተው ወደ ትውልድ አገርዎ መመለስ ከፈለጉ የመመለስ መብት አሎት::

- ለመመለስ ፍላጎታችሁን ያሳወቃችሁ ሁሉ ተጨማሪ መረጃዎችን ከአለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (ዶም) ተጨማሪ መረጃዎች ይሰጣችዋል:: ይኸው ድርጅት የመመለስ ሂደቱን የማከናውን ኃላፊነት ይወስዳል::

- በዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት (ዶም) ስር ያለውን በፍላጎት የሚመልስ ፕሮግራም በተመለከተ ተጨማሪ መረጃዎች እዚ ማግኘት ይችላሉ ::

**በመጨረሻ ወደ ጥገኝነት መስሪያ ቤት ሲመጡ መሳሪያ ፣ ስለት ወይም ሌሎች ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ቁሳቁሶች ፣ ፈንጂዎች ወይም ኬሚካሎች ፣ መርዛማ ንጥረ ነገሮች ይዞ መግባት እንደማይፈቅድ ልናሳውቅ እንወዳለን::**